የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
(ኢ.ብአአግ)

Ethiopian National United Patriotic Front
(ENUPF)

ነሐሴ 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

## ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ሰንደቅ ዓላማችን!

ሰንደቅ ዓላማችንን፣ ባንዲራችንን ያዋረዱትን እናወግዛለን!

ሰንደቅ ዓላማችን ወይም ባንዲራችን ለአገር አንድነትና ለወገን ኩራት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጭቁን ሕዝብና ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ምልክት ለመሆኗ ምስክሩ ምንም ዓይነት ባንዲራ ሳይኖራቸው በቅኝ ገዢዎች ሥር ከቆዩት አገሮች መካከል ነጻ ከወጡ በኋላ ብዙዎቹ የመርጡት የባንዲራ ቀለም አቀማመጡ ቢለያይም ወይም አንዳንድ ምልክቶች ቢጨመሩበትም የኢትዮጵያን አረንጓዴ ብጫ ቀይ ቀለም መሰረት በማድረግ ነው::

ዛሬ በአፍሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በእስያና በአውስትሬሊያ ማለትም በመላው ዓለም የሚገኙ ብዙ የጥቁር፣ የነጭና የብጫ ዘር ወጣቶችና ጎልማሶች የኢትዮጵያን ባንዲራ በጌጥነትና በኃይማኖት ዕምነት ምልክትነት በአካላቸው ላይ አጥልቀውት፣ በየልብሶቻቸው ላይ ለጥፈውት፣ በአንገታቸው ጠምጥመውትና በራሳቸው ላይ ደፍተውት ሲጓዙ ይታያሉ::

የኢትዮጵያ ባንዲራ ከኖህ የጥፋት ውሀ በኋላ እግዚአብሔር ምድርን ሁለተኛ በውሃ ማጥለቅለቅ አላጠፋትም ብሎ ለሰው ልጆች ቃል ኪዳን የገባበትን የቀስተ ደመና ምልክት ተከትሎ ከሰባቱ የቀስተ ደመና ቀለሞች ጎልተው የሚዩትን ሶስቱን አረንጓዴ፣ ብጫና ቀዩን ቀለም በመምረጥና የእግዚአበሔርን ቃል ኪዳን በመከተል የተመሰረተች መሆኗን ከመንፈሳዊው ዓለም ታሪክ እንረዳለን::

በአሁኑ ጊዜ በመንግሥታት ደረጃ ታውቀው በተባበሩት መንግሥታት ተመዝግበው ከሚገኙት 192 አገሮች መካከል ነጻነታቸውን ሳያስደፍሩ የራሳቸውን ባንዲራ በማውለብለብ ለብዙ ሺህ ዓመታት የኖሩት አገሮች 16 ብቻ ሲሆኑ ከነዚሁ አገሮች መካከል አረንጓዴ ብጫና ቀይ ወይም በማርያም መቀነት የምትመሰለውን ሰንደቅ

ዓላማዋን በማውለብለብ የኖረችና ከ16ቱ ነጻ አገሮች አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ ነች። ቅድስት ድንግል ማርያም በክርስትናው ዓለም የተወደደች የተከበረች የክርስቶስ እናት ስትሆን በእስልምናው ዓለምም ከሴቶች ሁሉ ተለይታ እሷ ብቻ በቅዱስ ቁርዓን ላይ በቅድስትነት የተጠቀሰች የነቢዩ ኢሳ እናት በመሆኗና በሌሎች እምነቶችም ያልተወገዘች ታላቅ እናት ነች። ስለዚህ የማርያም መቀነት የተሰኘው አባባል ማንንም አያስቀይምም።

ኢትዮጵያ የአውሮፓን ኮሎኒያሊስቶች፣ የቱርክና የግብጽን ወራሪዎች ስትከላከልና ስትቀጣ የኖረችው አረንጓዴ ብጫና ቀይ ባንድራዋን ሰንደቅ ዓላማ አድርጋ በመዝመት ነበረ። ይህችን ባንዲራችንን የሰዎችን እኩልነት የአገርን ነጻነት የሚቃወሙ ሁሉ ይጠሏታል። ሰንደቅ ዓላማችን ለአፍሪካ ነጻነትና አንድነት መነሻ ምልክት በመሆኗ ኮሎኒሊስቶች ያወግዟታል። አገርን በታትነው ሕዝብን ለያይተው እነሱ በየመንደሩ በየጎሳው ነግሰው ሕዝቡን እርስ በርሱ ለማስተላለቅ በጠላት የተቀጠሩ በሕዝብ ችግርና ስቃይ ለመደሰት የሚዘጋጁ ሁሉ ሰንደቅ ዓላማችንን በዋና ጠላትነት የፈርጅዋታል።

ለዚህም ግልጹ ማስረጃ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ከ1927 እስከ 1933 ዓ.ም. በነበረው አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ ከፈረንሳይ አገር በስተቀር በመላው ዓለም በሚገኙት በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ሲውለበሰቡ የነበሩት ሰንደቅ ዓላማዎች እየወረዱ እንዲጣሉ ተደርጎ ነበረ። ጅቡቲ በሚገኘው በኢትዮጵያ ቆንሲል የሚገኘውን ባንዲራችንን ለማውረድ በጅቡቲ የነበረው የጣሊይ ቆንሲል ሚሊቴሪ አታሼ የነበረው ሻለቃ ጥቂት የኢጣሊያ ወታደሮች አስከትሎ ወደኢትዮጵያ ቆንሲል በማምራት ላይ መሆኑን ያዩ አንድ የኦጋዴን ተወላጅ የሆነ ጀግና ኢትዮጵያዊ በጅቡቲ ነዋሪ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን በእሪታ መልክ ቀስቅሶ ሽሚዙን ቀድዶ ሕዝቡን አስከትሎ ቆመጥ ይዞ ጣሊያኖቹን ለመግጠም ኢትዮጵያ ቆንሲል ቢሮ ሲድርሰ በቢሮ ውስጥ የነበሩት ዋና ቆንሊል ልጅ አንዳርጋቸው መሳይ /ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይ/ በቆንሲሉ ቅጥር ግቢ ገብቶ ሰንደቅ ዓላማውነ ለማውረድ የሞከረውን ኢጣሊያን ሻለቃ በኮልት ሽጉጥ ደረቱን መትተው በመጣል ሰንደቀ ዓላማችንን አስከበረዋል። የቀሩትን ጣሊያኖች ሕዝቡ ሊጨርሳቸው በማሯሯጥ ላይ እያለ የፈረንሣይ ፖሊሶች ደርሰው በመገላገል በኢትዮጵያ ቆንሲል ግቢ የተገደለው ሻለቃ ደሙ ደመ ከልብ ሆኖ አስከሬኑ ወደ አገሩ ተልኳል። ልጅ አንዳርጋቸውም መብታቸው እንደተከበረ በስደት ወደ አውሮፓ ሄደዋል። በፈረንሳይ አገርም የዚያን ጊዜው ወጣት ተማሪ አክሊሉ ኃብተወልድ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በጠላት ወረራ ውስጥ ብትወድቅም ስንደቅ ዓላማዋ ፓሪስ በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ መውለብለቧ እንዳያ$ርጥ ሶስት አመት ሙሉ በመታገል አስከብረው ከቆዩ በኋላ በ1931 ዓ.ም. ጀርመን ፈረንሳይን በወረረበት ጊዜ የፈረንሳዮች ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ የኢትዮጵያም ሰንደቅ ዓላማ በኢምባሲው ማውለብለቡን አቁማ ቆዬች።

ሌላው አስደናቂ ታሪክ የተፈጸመዉ በዚያው በጣሊያን ወረራ ዘመን የኢጣሊያ ፋሽስት ወታደሮች በሮም አደባባይ የኢትዮጵያን ባንዲራ መሬት ላይ ጥለው ሲረጋግጡ የተመለከተው በጊዜው በሮም ነዋሪ የነበረው የትውልድ ሥፍራው ኤርትራ የነበረ ዘርዓይ ድረስ የተባለው ኢትዮጵያዊ ጀግና ጎራዴውን

መዝዞ የጣሊያኖቹን ቋንጃና ክንድ በመቆራረጡ ዜናው በመላው ዓለም ተደርሶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ክብር እንዲታወቅ አድርጎ ነበረ::

ዛሬ የነ ሙሶሎኒ አሽከሮች፣ ልጆችና የልጅ ልጆች ከባርነት ነጻ ያወጣቻቸውን የኢትዮጵያን ባንዲራ በኦፊሴል በማቃጠልና በመረጋገጥ ላይ ናቸው:: እነ አጼ ዩሐንስ የኢትዮጵያን ጦር እየመሩ ከደርቡሽ ጦር ጋር በመዋደቅ ላይ በነበሩበት ጊዜ አገር በቀል የነበረ ደጃዝማች ሰራይ የተባለ ኤርትራዊ አገሩን በመሸጥ ጣሊያንን እየመራ በ1881 ዓ.ም መላውን ኤርትራ ያስያዘ መሆኑን ታሪክ ያስረዳናል:: የዚሁ ባንዳ የልጅ ልጆች በዘር ጠላትነት ተሰልፈው በኢትዮጵያ ዙሪያ ገብ ጠላቶች ድጋፍ ኢትዮጵያን ከፋፍለው ዛሬ አንዱ በኢትዮጵያ ሌላው በኤርትራ የአገር መሪዎች በመባል የኢትዮጵያንና የኤርትራን ህዝብ እያሰቃዩት ነው::

ትላንት መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ባንዲራ የቆሎ መጠቅለያ ጨርቅ ነው በማለት አዋርዶ ተሳድቦ ወንድ በመጥፋቱ በባንዶች ታጅቦ በስልጣን ቆይ~ል:: ዛሬ ደግሞ የአጎቱ ልጅና የስልጣን አባቱ የሆነው ኢሳያስ አፈወርቂ የኤርትራ ህዝብ ተሳስቶ ከጌትነት ወደ ድህነት፣ ከነጻነት ወደ ባርነት የተመለሰበትን ቁልቁለት የ15ኛው ዓመት የነጻነት በዓል ተብሎ በአደባባይ በተከበረበት ዕለት የኢትዮጵያ ባንዲራ በእስረኝነት አደባባዩ መሃል ቀርቦ የተሰቀለበት ገመድ በእሳት ተቃጥሎ ከተበጠሰ በኋላ ሲወድቅ አጠገቡ የቆሙ ሁሉ እንዲረጋግጡት ተደርጓል:: የነ ቴዎድሮስ፣ የነዮሐንስ፣ የነሚኒሊክና የነተፈሪ ዘሮች የነገብርዬ፣ የነአሉላ፣ የነአበበ አረጋይ፣ የበላይ ዘለቀ፣ የነዘራይ ድረስና የእነ አብዲሳአጋ የጀግኖቹ ዘር ደክሞ የነክሪስፒ፣ የነሙሶሎኒ፣ የነግራዚያኒ አሽከሮች የነሰራይ፣ የነገብረ ልዑል የነ አስረስ ዘሮች ተባብረውና ተደራጅተው ባለፈው የሰሩት ግፍ ሁሉ አልበቃ ብሎአቸው የነጻነት፣ የአንድነትና የክብር ምልክታችን የሆነችውን ሰንደቅ ዓላማ ስትቃጠል የኢትዮጵያ ህዝብ በዝምታ ሊያልፈው አይገባም::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ያቃጠለውን የሻቢያ መንግሥት በጥብቅ ያወግዛል:: የኢትዮጵያን ጠላቶች በማንኛውም ዘዴ በየትኛውም አቅጣጫ ለመከላከልና ለማጥቃት ባለማ§ረጥ ይዘጋጃል:: ሰንደቅ ዓላማችንን ወይም ባንዲራችንን ያዋረዱ ሁሉ በቅርብ ቀን ይዋረዳሉ:: ያቃጠሉና የረጋገጡም ይረጋገጣሉ በጫሩት እሳት ይቃጠላሉ::

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ
ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዋን እያውለበለበች በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!